የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፴፮
አዲስ አበባ መጋቢት ፳፭ ቀን ፪ሺ፯

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

21st Year No 36
ADDIS ABABA 3rd April, 2015

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፰፻፹፩/፪ሺ፯ ዓ.ም

የሙስና ወንጀሎች አዋጅ......................ገጽ ፰ሺ፩፻፶፪

CONTENTS

Proclamation No. 881/2015

Corruption Crimes Proclamation…Page 8152

አዋጅ ቁጥር ፰፻፹፩/፪ሺ፯

## የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ

በ፲፱፻፺፮ ዓ.ም የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች ውስጥ በአፈፃፀም ወቅት የተስተዋሉ ግልጽነት የሚጎድላቸውን ድንጋጌዎች ግልጽ ማድረግና ማሻሻል በማስፈለጉ፤

የሙስና ወንጀሎቹ ማካተት የነበረባቸውን ተመሳሳይ ተግባራት በተለይም ከህዝብ የተሰባሰበ ወይም ለህዝብ ተብሎ የተሰባሰበ ሀብት በሚያስተዳድሩ የግል ዘርፍ አካላት የሚፈፀሙ ተመሳሳይ ተግባራትን በአግባቡ ያላካተቱ በመሆናቸው እነዚህኑ ማካተት በማስፈለጉ፤

ሀገራችን ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው የተባበሩት መንግስታት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽን እና የአፍሪካ ህብረት የሙስና መከላከያና መዋጊያ ኮንቬንሽን በግል ዘርፍ ተቋማት ውስጥ የሚፈፀሙ የጉቦኝነት፣ የምዝበራ እና ተመሳሳይ ተግባራት በሙስና ወንጀልነት መፈረጅ እንዳለባቸው በፈራሚ አገሮች ላይ ግዴታ የሚጥል በመሆኑ ሕጉን ከዚህ አኳያ ማሻሻል በማስፈለጉ፤

PROCLAMATION NO. 881/2015

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE CRIMES OF CORRUPTION

WEHREAS, it is found necessary to clarify and amend some provisions in the Criminal Code of the 2004 of the Federal Democratic Republic of Ethiopia relating to Corruption Crimes which are observed as unclear during their application;

WHEREAS, it has become necessary to include similar acts committed by the private sector particularly by those who administer funds collected from the public or collected for public purposes in the category of corruption offence;

WHEREAS, it has become necessary to categorize as corruption acts of bribery, embezzlement and other similar acts committed by the private sector as the United Nations Convention Against Corruption and the African Union Convention on Preventing and Combating Corruption which are ratified by Ethiopia impose such obligation on Member States;

በተግባር የታዩ ችግሮችን በመፍታት የተሟላ የህግ ማዕቀፍ እንዲኖር ማድረግ የፀረ ሙስና ትግሉን ለማጠናከር እና ሀገራችን ያለባትን አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ግዴታ በአግባቡ እንድትወጣ ለማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የሙስና ወንጀሎች በፈጣን ሁኔታ የመቀያየር ባህሪ ስላላቸው አጠቃላይ ወንጀሎችን በሚደነግገው የወንጀል ህግ (ኮድ) ውስጥ እንዲካተቱ ከማድረግ ይልቅ ራሱን በቻለ አዋጅ እንዲደነገጉ ማድረግ ተመራጭ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፭) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርእስ

ይህ አዋጅ "የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር ፰፻፹፩/፪ሺ፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፦

፩/ "የመንግስት መሥሪያ ቤት" ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግስት በጀት የሚተዳደር እና የፌደራል ወይም የክልል መንግስት ሥራዎች የሚከናወኑበት ማናቸውም መሥሪያ ቤት ነው፤

፪/ "የመንግስት ሠራተኛ" ማለት በመንግስት መሥሪያ ቤት ወይም በመንግስት የልማት ድርጅት ውስጥ ተቀጥሮ፣ ተሹሞ፣ ተመድቦ፣ ወይም በህዝብ ተመርጦ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ሥራን የሚያከናውን ማንኛውም ሰው ሲሆን የሥራ አመራር ቦርድ አባልን ይጨምራል፤

፫/ "የመንግስት የልማት ድርጅት" ማለት የመንግስት የባለቤትነት ድርሻ በሙሉ ወይም በከፊል ያለበት የፌደራል ወይም የክልል መንግስት የልማት ድርጅት ወይም የአክሲዮን ማህበር ነው፤

WHEREAS, it is found necessary to rectify practical problems observed by enacting comprehensive legislation to strengthen the fight against corruption and to enable Ethiopia so as to discharge its continental and global obligations;

WEHEREAS, it is found necessary to address corruption offences in a separate proclamation rather than make them part of the Criminal Code due to fast changing nature of the offences;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (5) of the Constitution of the Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## PART ONE

## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Corruption Crimes Proclamation No. 881/2015".

### 2. Definition

In this Proclamation unless the context otherwise requires:

1/ "public office" means any office which undertakes federal or regional government activities and gets its budgets fully or partly from government;

2/ "public servant" means any person who is employed, appointed or elected to work either temporarily or permanently in a public office or public enterprise and includes member of a management board;

3/ "public enterprise" means any federal or regional public enterprise or share company which is fully or partly owned by government;

፬/"ህዝባዊ ድርጅት" ማለት በማንኛውም አግባብ ከአባላት ወይም ከህዝብ የተሰበሰበ ወይም ለህዝባዊ አገልግሎት ታስቦ የተሰበሰበ ገንዘብ፣ ንብረት ወይም ሌላ ሀብትን የሚያስተዳድር አካልንና አግባብነት ያለው ኩባንያን የሚያካትት የግል ዘርፍ ሲሆን፣ የሚከተሉትን አያካትትም፦

ሀ) የሃይማኖት ድርጅትን፤

ለ) የፖለቲካ ድርጅትን (ፓርቲን)፤

ሐ) የዓለም አቀፍ ድርጅትን፤ እና

መ) ዕድርንና ተመሳሳይ ባህላዊ ወይም ሃይማኖታዊ ይዘት ያለው ማህበርን።

4/ "public organization" means any organ in the private sector which in whatever way administers money, property or any other resource collected from members or from the public or any money collected for the benefit of the public which includes appropriate company, but does not include:

a) religious organization;

b) political party;

c) international organization;and

d) edir or other similar traditional or religious associations.

፭/ "የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ" ማለት በህዝባዊ ድርጅት ውስጥ ተቀጥሮ፣ ተመድቦ፣ ወይም በአባላት ተመርጦ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት የሚሠራ ሰራተኛ ሲሆን የድርጅቱን መሪ፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባልን፣ የአክሲዮን ማህበር ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅት የሚያደራጅ ሰውን ወይም ኮሚቴን ያካትታል፤

5/ "employee of a public organization" means an employee who is employed, appointed or elected by members to work either temporarily or permanently in a public organization and include leader of the organization,any member of the board of directors or any person or committee involved in the formation of a share company or a charity;

፮/ "አግባብነት ያለው ኩባንያ" ማለት በሕዝባዊ ድርጅት የተቋቋመ ኃላፊነቱ የተወሰነ ኩባንያ ሲሆን እንደዚህ ዓይነት ኩባንያ ከሌሎች ጋር የሚያቋቋመውን የሽርክና ማኅበርን ያጠቃልላል፤

6/ "appropriate company" means any private limited company which is established through the contribution of shares by public organizations and includes joint venture established by such company in association with others;

፯/ "ለህዝባዊ አገልግሎት የተሰበሰበ ሀብት" ማለት የተወሰነን የህብረተሰብ ክፍልን ወይም ህብረተሰቡን በአጠቃላይ ለመርዳት ወይም ለመደገፍ ወይም ለማበረታታት ወይም ለማልማት ታስቦ የተሰበሰበ ወይም ለዚሁ ዓላማ እንዲውል በማንኛውም መንገድ የተገኘ እና በበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የሚተዳደር ወይም የሚንቀሳቀስ ገንዘብ፣ ንብረት ወይም ሀብት ነው፤

7/ "resource collected for the benefit of the public" means any money, property or resource that is collected with the intent to support, assist, encourage or develop the whole or a section of the community or obtained in any way with such intent and administered or utilized by a charity or association;

፰/ "የበጎ አድራጎት ድርጅት" ማለት አግባብ ባለው ህግ መሰረት የተመዘገበ ሆኖ ለበጎ አድራጎት ዓላማ ብቻ የተቋቋመና ለህዝብ ጥቅም የሚሰጥ ተቋም ነው፤

8/ "A Charity" means an institution, which is legally registered and established exclusively for charitable purposes and gives benefit to the public;

፱/ "የሃይማኖት ድርጅት" ማለት የአንድ ሃይማኖት ተከታዮች ሃይማኖታቸውን ለማደራጀት እና ለማስፋፋት የሚያቋቁሙት ተቋም ወይም ቤተ እምነት ሲሆን የበጎ አድራጎት ዓላማዎችን

9/ "religious organization" means an organization or institution of worship established by the followers of a religion to organize or to promote their religion but shall

ለማሳካት በሃይማኖት ድርጅቱ የተቋቋሙ ድርጅቶችን አያጠቃልልም፤

፲/ "የፖለቲካ ፓርቲ" ማለት አግባብ ባለው ህግ መሰረት የተዘመገበ እና የፖሊቲካ አጀንዳ የሚያራምድ ድርጅት ነው፤

፲፩ "ዓለም አቀፍ ድርጅት" ማለት የኢትዮጵያ መንግስት ከሌላ አገር መንግስት ወይም ከዓለም አቀፍ ወይም አህጉራዊ ተቋም ጋር በሚያደርገው ስምምነት መሠረት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚንቀሳቀስ ዓለም አቀፍ ተቋም ወይም የውጭ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ነው፤

፲፪/ "በጊዜያዊነት ሥራን የሚያከናውን ሰው" ማለት በቋሚነት ሳይቀጠር በክፍያ ወይም ያለክፍያ በሙሉ ጊዜ ወይም በትርፍ ጊዜ የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግስት ልማት ድርጅት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራን የሚያከናውን ሰው ሲሆን ተለማማጅ ሰራተኛን ያካትታል፤

፲፫/ "ጥቅም" ማለት የሚከተሉትን ያካትታል፦

ሀ) በገንዘብ ወይም በማናቸውም ዋጋ ባለው መያዣ ወይም በሌላ ንብረት ወይም በንብረት ላይ ያለን ጥቅም (መብት)፤

ለ) ማንኛውንም ሹመት፣ ቅጥር ወይም ውል፤

ሐ) ብድርን፣ ግዴታን ወይም ማናቸውንም ዕዳ በሙሉም ሆነ በከፊል መክፈልን፣ ማስቀረትን፣ ማወራረድን፣ ወይም ከእነዚህ ነገሮች ነፃ ማድረግን፤

መ) ከተመሰረተ ወይም ካልተመሰረተ የአስተዳደር፣ የፍትሐ ብሔር ወይም የወንጀል ክስ ወይም ካስከተለው ወይም ከሚያስከትለው ማናቸውም ቅጣት ወይም የችሎታ ማጣት በማዳን ወይም ይህን በመሰለ ዘዴ የሚደረግን አገልግሎት ወይም ውለታ፤

ሠ) ማናቸውንም መብት ወይም ግዴታ መፈጸምን ወይም ከመፈጸም መታቀብን፤

ረ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ሠ) ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች ውጭ በገንዘብ የማይተመን ማናቸውንም ሌላ ጥቅም ወይም አገልግሎት፤ እና

not include the organizations established under the religious organization with intent to achieve objectives of a charity;

10/ "political party" means an organization registered under relevant laws of the country to promote political agenda;

11/"international organization" means an international entity or foreign charity or association that undertakes activities within Ethiopia based on agreements concluded between Ethiopia and other governments or international or regional organizations;

12/ "temporary worker" means a person who works for gain or without gain full time or part time without being a permanent worker in a government office or public enterprise or public organization and includes apprentice workers;

13/ "advantage" means include

a) any interest or right in money or in another valuable item or property;

b) any appointment, employment or contract;

c) paying, relieving, or making free from loan, obligation or any other liability fully or partly;

d) any service or favour intended to relieve from any actual or potential civil, administrative or criminal suit and liabilities or incapacities resulting there from;

e) any discharge or abstention from exercising a right or an obligation;

f) any other interest or service other than those enumerated in this sub article from paragraph (a) to (e) that cannot be expressed in monetary terms;

ሰ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ረ) ከተጠቀሱት ጥቅሞች አንዱን ማቅረብን፣ ጥቅሙ የሚገኝበትን መንገድ ማመቻቸትን ወይም ይህንኑ በሚመለከት የተስፋ ቃል መግባትን ወይም መቀበልን።

፲፬/"የማይገባ ጥቅም" ማለት ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ወይም አግባብ ባልሆነ መንገድ የተገኘ ጥቅም ነው፤

፲፭/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፮/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል።

## ፫. ጥቅም የማግኘት ወይም የመጉዳት የሐሳብ ግምት

ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በስተቀር የሙስና ወንጀሎቹ የተፈፀሙት የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም ሌላውን ሰው ለመጉዳት መሆኑ በተደነገገ ጊዜ በድንጋጌው የተመለከተው ግዙፋዊ ፍሬ ነገር መፈጸሙ ከተረጋገጠ ድርጊቱ የተፈፀመው ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራስ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም የሦስተኛ ወገንን መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት እንደሆነ ይገመታል።

## ፬.መርህ

፩/ ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተመለከተውን የሙስና ባህርይ የሚያሟላ ወንጀል በፈጸመ ጊዜ ለወንጀሉ የተደነገጉት የቅጣት ድንጋጌዎች ይፈፀሙበታል።

፪/ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የማይገባ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ በተሰጠው ኃላፊነት ወይም ተግባር ማድረግ የሚገባውን እንዳያደርግ ወይም ማድረግ የማይገባውን እንዲያደርግ ከሌላ ሰው ላይ ጥቅም የተቀበለ ወይም የጠየቀ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም ለማስገኘት የተሰጠውን ስልጣን ወይም የህዝብ አደራ ያላግባብ የተገለገለበት እንደሆነ፤ ወይም ጥቅም ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው

g) providing any of the benefits enumerated from paragraph (a) to (f) of this sub-article or facilitating the methods with such intent or making promises for such purposes.

14/ "undue advantage" means an improper benefit or a benefit obtained through inappropriate means;

15/ "person" means natural or juridical person;

16/any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. Presumption of Intent to Obtain Advantage or to Injure

Unless evidence is produced to the contrary, where it is proved that the material element (the act) has been committed as defined in a particular provision providing for a crime of corruption perpetrated to obtain or procure undue advantage or to cause injury of another person, such act shall be presumed to have been committed with intent to obtain for oneself or to procure for another an undue advantage or to injure the right or interest of a third person.

## 4. Principle

1/ Any public servant or employee of a public organization or any other person who commits any one of the offenses characterized as corruption in Sub-Article 2 of this Article shall be subject to the punishments prescribed for such offences.

2. Any public servant or employee of public organization who, with intent to obtain for himself or to procure for another an undue advantage or to injure the right of another, directly or indirectly, accepts or solicits an undue advantage by performing his responsibility or duty improperly; or who, in any other way, misuses the responsibility or public trust vested in him to procure an undue advantage for himself or another; or

Any person who, with intent to obtain for himself or to procure for another an undue advantage or to injure the right of another,

ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ ለመንግስት ወይም ለህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለመስጠት ቃል የገባ፣ ያቀረበ፣ የሰጠ ወይም ለማቅረብ የተስማማ እንደሆነ፤ ወይም በአግባቡ ለተፈፀመ ወይም በአግባቡ ለወደፊቱ ለሚፈፀም የመንግስት መሥሪያ ቤት ወይም የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራ የማይገባ ጥቅም ለማንኛውም ሰው የሰጠ ወይም ከማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የተቀበለ እንደሆነ፤ በሙስና ወንጀል ፈፃሚነት ተጠያቂ ይሆናል።

promises, offers, gives or agrees to give an undue advantage to a public servant or employee of public organization; or
Any person, who gives, or any public servant or employee of public organization, who accepts, an undue advantage in consideration for an act of public office, public enterprise or public organization properly performed or to be performed, shall be deemed to have committed crimes of corruption and be liable to the punishments prescribed.

፫/ ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ፦

ሀ) በተጣሰው የሙስና ወንጀል ድንጋጌ ከሚወሰንበት ቅጣት በተጨማሪ በሕገ ወጥ መንገድ ያገኘው ጥቅም፣ ገንዘብ ወይም ንብረት እንዲሁም ጥቅሙን፣ ገንዘቡን ወይም ንብረቱን በማሰማራት የተገኘው ትርፍ ወይም ወለድ እንዲወረስ ወይም ጥቅሙ፣ ገንዘቡም ሆነ ንብረቱ ካልተገኘ የወንጀል ውጤት ካልሆነ ሀብቱ ተመጣጣኝ ዋጋው ተወርሶ እንዲመለስ ይደረጋል፤

ለ) በሙስና ወንጀሉ ምክንያት ያገኘው ጥቅም ባይኖርም በመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግስት ልማት ድርጅት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ሀብት ላይ ጉዳት ማድረሱ ከተረጋገጠ ካደረሰው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ዋጋ ተወርሶ በማካካሻነት እንዲከፍል ይደረጋል።

3/ Any public servant or employee of a public organization convicted of corruption crime shall, in addition to the punishment under the infringed provision:

a) forfeit the profit, interest, money or property unlawfully obtained or pay its equivalent value where the profit or property is not found;

b) pay compensation proportionate to the damage sustained by the public office or public organization or public enterprise although he has not obtained any advantage from the offence of corruption.

፬/ ማንኛውም ሰው ከመንግስት ሠራተኛ ወይም ከህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ጋር ባለው ግንኙነት ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ያገኘ ወይም በመንግስት መሥሪያ ቤት፣ በመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ሀብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ያደረገ እንደሆነ እንደአግባቡ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆኑበታል።

4/ The provisions of paragraphs (a) and (b) of sub-article (3) of this Article shall apply to anyone who obtains undue advantage or causes damage to the property of a public office, public enterprise or public organization due to his relationship with a public servant or employee of a public organization.

## ፭. የህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በሙስና ወንጀል ተጠያቂነት

በወንጀል ህጉ አንቀፅ ፺ (፫) የተደነገገው ቢኖርም የመንግስት የአስተዳደር አካላትን ሳይጨምር የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በሙስና ወንጀል ተካፋይ ሆኖ ሲገኝ የድርጅቱ ኃላፊዎች ወይም ሠራተኞች በየግላቸው መጠየቃቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

፩/ በቀላል እስራት ለሚያስቀጣ ለእያንዳንዱ የቅጣት ዓመት ሃያ ሺህ ብር፤

፪/ ከ፭ ዓመት በታች ፅኑ እስራት ለሚያስቀጣ ለእያንዳንዱ የቅጣት ዓመት ሰላሣ ሺህ ብር፤

፫/ ከአምስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት ፅኑ እስራት ለሚያስቀጣ ለእያንዳንዱ የቅጣት ዓመት ሃምሳ ሺህ ብር፤

፬/ ከአስር ዓመት በላይ ፅኑ እስራት ለሚያስቀጣ ለእያንዳንዱ የቅጣት ዓመት ሰማንያ ሺህ ብር፤መቀጮ እንዲከፍል ይወሰንበታል።

## ፮. ከፍትሕ ስለማምለጥ

፩/ ማንኛውም ሰው፦

ሀ) የሙስና ወንጀል በመፈፀሙ በፍትህ አካል እየተፈለገ መሆኑን እያወቀ፤ወይም ተፈላጊ መሆኑን የሚገልፅ ማስታወቂያ መውጣቱን እያወቀ ወይም በዋስ ከተለቀቀ በኋላ ከፍትህ ያመለጠ እንደሆነ፤ ወይም

ለ) ፖሊስ ወይም መርማሪ ሊይዘው ወይም ሊጠራው መምጣቱን አውቆ ወይም ከተያዘ ወይም በቁጥጥር ሥር ከዋለ በኋላ ያመለጠ እንደሆነ፤

በተገኘበት ወቅት በሕግ መሰረት ለፍትህ መቅረቡ ወይም በሌለበት የተፈረደበት የእስር ቅጣት ተፈፃሚ መሆኑ እና በሙስና ወንጀል ምክንያት መወረስ የሚገባው ሀብት መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ ከፍትህ በማምለጡ ብቻ በተከሰሰበት ወንጀል ለተፈረደበት ለእያንዳንዱ ዓመት ከሃያ ሺህ ብር በማያንስ ከሰባ ሺህ ብር በማይበልጥ በተጨማሪነት እንዲከፍል ይወሰንበታል::

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚወሰነው መቀጮ ጥፋተኛው ባይገኝም ሊገኝ ከሚችል ሀብቱ እንዲከፈል ይደረጋል።

## 5. Criminal Liability of Juridical Persons for Crimes of Corruption

Notwithstanding the provisions of Article 90 (3) of the Criminal Code, without prejudice to individual responsibility of the officials or employees, a juridical person other than administrative authorities involved in crimes of corruption shall be punishable with:

1/ a fine of Birr twenty thousand for each year of penalty for crimes punishable with simple imprisonment;

2/ a fine of Birr thirty thousand for each year of penalty for crimes punishable with rigorous imprisonment not exceeding five years;

3/ a fine of Birr fifty thousand for each year of penalty for crimes punishable with rigorous imprisonment from five years to 10 years;

4/ a fine of Birr eighty thousand for each year of penalty for crimes punishable with rigorous imprisonment exceeding ten years.

## 6. Running Away from Justice

1/ Whosoever:

a) becomes a fugitive with full knowledge that he being looked for by justice organs or after issuance of a notice or after his release on bail in connection with crimes of corruption; or

b) dis-appears with full knowledge of an impending arrest or issues of summons by a police officer, investigator or disappears after arrest or detention.

without prejudice to bringing him to court when found, or the enforcement of the imprisonment or the sequestration of the property on grounds of corruption imposed in his absence is punishable with a fine of not less than Birr twenty thousand and not exceeding Birr seventy thousand for each penality year imposed.

2/ The fine imposed under sub-article (1) of this Article shall be collected from the property of the convict even if he is not found.

፯. <u>የአስተዳደር ቅጣትና የፍትሐ ብሔር ኃላፊነት በተጻራቢነት ተፈጻሚ ስለመሆናቸው</u>

በሙስና ወንጀል ተከሶ መቀጣት ወይም በነፃ መለቀቅ በአስተዳደርም ሆነ ወይም በፍትሐ ብሔር ተጠያቂ መሆንን አያስቀርም።

፰. <u>ከክስ ነፃ ማድረግ</u>

፩/ ማንኛውም ሰው ከሙስና ወንጀሎች በአንዱ ተካፋይ ከሆነ በኋላ ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት ስለተፈፀመው ድርጊትና ስለተካፋዮቹ ሚና ጠቃሚ መረጃ ከሰጠ በሕግ ስልጣን በተሰጠው አካል በሙስና ወንጀል እንዳይከሰስ ሊደረግ ይችላል።

፪/ ስለመረጃው ጠቃሚነት አወሳሰንና ድርጊቱን ያጋለጠው ሰው እንዳይከሰስ ስለሚደረግበት ሁኔታ የሚደነግጉ ልዩ ሥነ-ሥርዓቶች አግባብ ባለው የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ ይወሰናሉ።

፫/ ሕጋዊ በሆነ መልኩ ላገኘው ወይም ሊያገኘው ለሚገባ አገልግሎት የሰጠውን ማናቸውንም ጥቅም እንደሰጠ ላጋለጠ ሰው የሰጠው ጉቦ ወይም ስጦታ ወይም ዋጋ ያለው ነገር በወንጀሉ ምክንያት ከተወረሰው ንብረት ላይ ይመለስለታል።

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>የሙስና ወንጀል ድንጋጌዎች</u>

፱. <u>በሥልጣን አላግባብ መገልገል</u>

፩/ ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ፦

ሀ) የተሰጠውን ሹመት፣ ሥልጣን ወይም ኃላፊነት በግልፅ ተግባር ወይም በግድፈት ያለአግባብ የተገለገለበት እንደሆነ፤

ለ) በግልፅ ከተሰጠው ሥልጣን ወይም ኃላፊነት አሳልፎ የሠራ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ) ሥልጣኑ ወይም ኃላፊነቱ የማይፈቅድለትን ጉዳይ፣ በተለይም ሥልጣን ወይም ኃላፊነት ሳይኖረው ወይም ከሥራው ከታገደ፣ ከተዛወረ፣ ከተሻረ ወይም ሥልጣኑን ወይም

7. <u>**Concurrent Application of Administrative Penalities and Civil Liability**</u>

Conviction or acquittal under the provisions of this Proclamation shall not exclude liability for civil damages and administrative penalities.

8. <u>**Exemption from Prosecution**</u>

1/ Whoever, having taken part in a corruption crime, supplies vital information on the crime committed and the role of participants therein, before the matter is taken to Court, may be exempted by the competent organ from prosecution of corruption offence

2/ Special procedures shall be laid down in the relevant criminal procedure laws concerning the assessment of the vitality of the information and the conditions for exemption from prosecution of the person who has disclosed the crime.

3/ The bribe, gift or valuable thing a person has given in consideration for service he has lawfully obtained or is entitled to obtain shall be restored to him out of the property forfeited to the State on account of the crime, where he has disclosed his act of giving such an advantage.

<u>**PART TWO**</u>

<u>**CORRUPTION OFFENCES**</u>

9. <u>**Abuse of Power or Responsibility**</u>

1/ Any public servant or employee of a public organization who, with intent to obtain for himself or to procure for another an undue advantage or to injure the right or interest or advantage of another:

a) misuses his official position or the power or responsibility entrusted to him, whether by a positive act or by a culpable omission;

b) exceeds the power or responsibility with which he is officially vested;

c) performs official acts when he is not, or is no longer, qualified to do so, especially in the case or in consequence of incompetence, suspension, transfer,

ኃላፊነቱን ከተወ በኋላ የሠራበት እንደሆነ፤ እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት እና ከሦስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከአሥር ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፪/ ኃላፊነቱ ወይም ግዴታው እንዲጣስ የተፈለገበት ዓላማ፣ የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት፣ የጥፋተኛው የኃላፊነት ወይም የሥልጣን ደረጃ ወይም በግለሰብ፣ በመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ጥቅም ወይም በህዝብ ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛነት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተፈጸመውን ወንጀል ከባድ አድርጎት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከሰባት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ፅኑ እስራት እና ከአስር ሺህ ብር እስከ አንድ መቶ ሺህ ብር የሚደርስ መቀጮ ይሆናል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፪) ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ሁለቱ ወይም ከዚያ በላይ ተደራርበው ሲገኙ፣ ቅጣቱ ከአስር ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት የሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከሃያ ሺህ ብር እስከ ሁለት መቶ ሺህ ብር የሚደርስ መቀጮ ይሆናል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተገለፀው ቢኖርም በህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የሚፈፀም ከሰው ሃይል አስተዳደር ጋር የተያያዘ ጥፋት ጉቦ የመስጠትና የመቀበል ሁኔታ መኖሩ ካልተረጋገጠ በስተቀር በሙስና ወንጀል አያስከስስም፡፡

**፲. ጉቦ መቀበል**

፩/ ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራ ግዴታው ማድረግ የማይገባውን ለማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባውን ላለማድረግ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም እንዲሰጥ የጠየቀ፣ የተቀበለ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ፣ እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት እና ከሦስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ፣ ወይም ከአስር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከአርባ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

removal from office or its cessation; shall be punishable, according to the circumstances of the case with simple imprisonment for not less than one year and fine not less than Birr three thousand, or with rigorous imprisonment not exceeding ten years and fine not exceeding Birr ten thousand.

2/ Where the purpose of the breach of responsibility or duty solicited, the extent of the advantage received in consideration, degree of the responsibility or powers of the culprit or the extent of the harm to private, public or State interests or advantage renders the crime committed under sub-article (1) of this Article of particular gravity, the punishment shall be rigorous imprisonment from seven years to fifteen years and fine not less than Birr ten thousand and not exceeding Birr hundred thousand.

3/ Where two or more of the circumstances mentioned in sub-article (2) of this Article are found concurrently, the punishment shall be rigorous imprisonment from ten years to twenty five years and fine not less than Birr twenty thousand and not exceeding Birr two hundred thousand.

4/ Notwithstanding the provisions under sub-article (1) and (2) of this Article acts committed by an employee of a public organization in connection with human resource administration shall not be considered as corruption offence unless the involvement of bribes are confirmed.

**10. Bribery**

1/ Any public servant or employee of a public organization directly or indirectly, seeks, receives or exacts a promise of an advantage for himself or another, in order to act or refrain from acting, in violation of the duties proper to his office, shall be punishable with simple imprisonment for not less than one year and fine not less than Birr three thousand or rigorous imprisonment not exceeding ten years and fine not exceeding Birr forty thousand.

፪/ ኃላፊነቱ ወይም ግዴታው እንዲጣስ የተፈለገበት ዓላማ፣ የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት፣ የጥፋተኛው የኃላፊነት ወይም የሥልጣን ደረጃ ወይም በግለሰብ፣ በመንግስት፣ ወይም በህዝባዊ ድርጅት ጥቅም ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛነት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተፈጸመውን ወንጀል ከባድ አድርጎት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከሰባት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ፅኑ እስራት እና ከአስር ሺህ ብር የማያንስ ከአንድ መቶ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል።

፫/ ወንጀሉን የፈጸመው በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፪) ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ሁለቱ ወይም ከዚያ በላይ ተደራርበው ሲገኙ ቅጣቱ ከአስር ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት የሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከሃያ ሺህ ብር እስከ ሁለት መቶ ሺህ ብር የሚደርስ መቀጮ ይሆናል።

፬/ ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) በተገለፀው መሠረት ወንጀሉን የፈጸመው ከዓለም አቀፍ ግብይት ወይም ግንኙነት ጋር በተያያዘ የሥራ ግዴታ ድንበር ዘለል ኮርፖሬሽንን ጨምሮ ከማንኛውም የሌላ አገር መንግስት፣ ድርጅት፣ ሰው ወይም ዓለም አቀፍ ድርጅት ጥቅም ወይም ስጦታ የጠየቀ፣ የተቀበለ ወይም ለመቀበል የተስማማ እንደሆነ፣ እንደነገሩ ሁኔታ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፪) ወይም (፫) ከተመለከቱት ቅጣቶች በአንዱ ይቀጣል።

## ፲፩.የማይገባ ጥቅም መቀበል

፩/ ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት ማድረግ የሚገባውን ተግባር ለማከናወን ሲል ይህንኑ ተግባር ከመፈፀሙ በፊት ወይም ከፈፀመ በኋላ ጥቅም እንዲሰጠው የጠየቀ፣ ያገኘ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ፣ እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት እና ከሦስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከሃያ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

2/ Where the purpose of the breach of responsibility or duty solicited, the extent of the advantage received, the degree of responsibility or powers of the culprit or the, extent of harm to private, public or State interests or advantages renders the crime committed under sub-article (1) of this Article of particular gravity, the punishment shall be rigorous imprisonment from seven years to fifteen years and fine not less than Birr ten thousand and not exceeding Birr hundred thousand.

3/ Where two or more of the circumstances mentioned in sub-article (2) of this Article are present concurrently, the punishment shall be rigorous imprisonment from ten years to twenty-five years and fine not less than Birr twenty thousand and not exceeding Birr two hundred thousand.

4/ Any public servant or employee of a public organization who, in the manner specified under sub-article (1) of this Article, and in respect of his duty connected with international trade or transaction, solicits, accepts or agrees to accept advantage or a gift from any foreign State, person or organization, including a trans-national corporation shall, according to the circumstance of the case, be liable to one of the punishments prescribed in sub-articles (1), (2) or (3) of this Article.

## 11. Acceptance of Undue Advantages

1/ Any public servant or employee of a public organization who, for the performance of an act proper to his office, solicits or obtains an advantage or exacts a promise before or after the performance of such an act, shall be punishable, according to the circumstances of the case, with simple imprisonment for not less than one year, or with rigorous imprisonment not exceeding seven years and fine not less than Birr three thousand and not exceeding Birr twenty thousand.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በተፈጸመው ወንጀል የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት፣ የጥፋተኛው የኃላፊነት ወይም የሥልጣን ደረጃ የወንጀሉን አፈጻፀም ከባድ አድርጎት እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ፅኑ እስራት እና ከአምስት ሺህ ብር በማያንስ ከስልሳ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይሆናል፡፡

፫/ ወንጀሉ የተፈፀመው ከዓለም አቀፍ ግብይት ወይም ግንኙነት ጋር በተያያዘ የሥራ ኃላፊነት ወይም ግዴታ እንደሆነ፤ እንደነገሩ ሁኔታ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) መሠረት ያስቀጣል፡፡

## ፲፪. <u>አስታራቂ ሽማግሌዎችና ሌሎች ሰዎች የሚፈፅሙት ጉቦ የመቀበል ወንጀል</u>

፩/ ማንኛውም አስታራቂ ሽማግሌ፣ የግልግል ዳኛ፣ የፍርድ ቤት ነባሪ፣ ንብረት ጠባቂ፣ ወይም አጣሪ፣ ሥራውን ለማካሄድ በባለስልጣን የተሾመ ተርጓሚ ወይም አስተርጓሚ ወይም በዳኝነት ወይም በዳኝነት ነክ በሚታይ ጉዳይ ላይ በሙያው ረገድ አስተያየቱን ወይም የምስክርነት ቃሉን የሚሰጥ ማንኛውም ልዩ አዋቂ (ኤክስፐርት)፣ ወይም ገቢና ወጪን ኦዲት የሚያደርግ ኦዲተር፣ ወይም ግንባታ በተገባው ውል መሰረት መከናወኑን የሚያረጋግጥ መሃንዲስ ማድረግ የሚገባውን ላለማድረግ ወይም ማድረግ የማይገባውን ለማድረግ ጉዳዩ ከሚመለከተው ሰው ላይ ጥቅም እንዲሰጠው የጠየቀ ወይም የተቀበለ እንደሆነ፣ እንደነገሩ ሁኔታ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፲ (፩)፣ (፪) ወይም (፫) ከተመለከቱት ቅጣቶች በአንዱ ይቀጣል፡፡

፪/በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀጽ (፩) ከተመለከቱት ሰዎች አንዱ በተሰጠው ኃላፊነት ወይም ተግባር መሠረት ማድረግ የሚገባውን ተግባር ለማከናወን ሲል ይህንኑ ተግባር ከመፈፀሙ በፊት ወይም ከፈፀመ በኋላ ጥቅም እንዲሰጠው የጠየቀ ወይም የተቀበለ እንደሆነ፣ እንደነገሩ ሁኔታ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፲፩ (፩) ወይም (፪) ከተመለከቱት ቅጣቶች በአንዱ ይቀጣል፡፡

2/ Where the extent of the advantage, received or the degree of responsibility or power of the person corrupted renders the crime committed under sub-article (1) of this Article of particular gravity, the punishment shall be rigorous imprisonment from five years to fifteen years and fine not less than five thousand Birr and not exceeding sixty thousand Birr.

3/ Where the crime is committed in respect of a duty connected with international trade or transaction, the punishment prescribed in the sub-articles (1) or (2) of this Article shall be applicable, according to the circumstances of the case.

## 12. <u>Corruption Committed by Arbitrators and Other Persons</u>

1/ Any conciliator, arbitrator, juror, trustee or liquidator, translator or interpreter engaged by the public authorities in their technical capacity or expert testifying before or giving his opinion to judicial or quasi-judicial proceedings or auditor or auditing incomes and expenditures or an engineer who verifies the construction according to the agreement, who solicits or accepts an advantage or gift from a person interested in the matter, in consideration for the performance or omission of an act in violation of the duties entrusted to him shall be punishable, according to the circumstances of the case, with one of the penalties prescribed under Article 10 (1), (2) or (3) of this Proclamation.

2/ Whenever any one of the persons mentioned under sub-article (1) solicits or accepts an advantage or gift, before or after performing an act entrusted to him, he shall, according to the circumstances of the case, be punishable with one of the penalties prescribed under Article 11 (1) or (2) of this Proclamation.

## ፲፫. የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራን በማያመች አኳኋን መምራት

፩/ ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት፣ ወይም ለማስገኘት በማሰብ ሥልጣኑን ወይም ሃላፊነቱ ተጠቅሞ፦

ሀ) በንግድ ወይም በሌላ ሥራ፣ በግዢ ወይም በሽያጭ ወይም ከሚያከናውነው ሥራ ጋር በተያያዘ በማናቸውም የሥራ ግንኙነት ማናቸውም ዓይነት ጥቅም የወሰደ ወይም ይህን ጥቅም የሚያገኝበትን ውል የተዋዋለ ወይም ሌላ ዘዴ የፈጠረ እንደሆነ፤

ለ) አግባብ ባለው ባለሥልጣን ወይም ኃላፊ ከተወሰነው በላይ በሆነ ዋጋ የዕቃ ማቅረብ ውል፣ የሥራ መቋረጥ ውል ወይም ማናቸውም የሥራ ውል የተዋዋለ ወይም በውል ከተመለከተው ዕቃ ወይም አገልግሎት ውጭ የተቀበለ እንደሆነ፤

ሐ) በጠቅላላው በሥራው ሥልጣን ወይም ኃላፊነት መሠረት በአደራ የተሰጠውን ወይም ሊጠብቀውና ሊከላከለው የሚገባውን የመንግስት መሥሪያ ቤት፣ የመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ጥቅም የሚጎዳ ተግባር በማናቸውም ዘዴ የፈፀመ እንደሆነ፤

እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት እና ከሦስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአስር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከአንድ መቶ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

፪/ ኃላፊነቱ ወይም ግዴታው እንዲጣስ የተፈለገበት ዓላማ፣ የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት፣ የጥፋተኛው የኃላፊነት ወይም የሥልጣን ደረጃ ወይም በግለሰብ፣ በህዝባዊ ድርጅት፣ በመንግስት ወይም በህዝብ ጥቅም ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛነት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተፈጸመውን ወንጀል ከባድ አድርጎት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከሰባት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ፅኑ እስራት እና ከአስር ሺህ ብር የማያንስ ከሁለት መቶ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል።

## 13. Maladministration of Government or Public Enterprise work

1/ Any public servant or employee of a public organization who, with intent to obtain for himself or to procure for another an undue advantage, and by using his power or responsibility:

a) improperly takes or ensures for himself, by concluding a contract or by devising other means, an advantage in a business or other undertaking, a sale or a purchase, or any other transaction related with his duty;

b) concludes a contract of material supply or termination of public works contract or any other transaction at a price higher than that fixed by the competent authority or receives goods or services other than those specified in the contract; or

c) in general, by any means, injures the interests of the public office, public enterprise or public organizations entrusted to his charge and which it is his duty to protect;

shall be punishable with simple imprisonment not less than one year and a fine not exceeding Birr three thousand or rigorous imprisonment not exceeding ten years and fine not exceeding Birr one hundred thousand.

2/ Where, the purpose of the breach of responsibility or duty solicited, the extent of the advantage received, the degree of responsibility or powers of the culprit or the extent of the harm to private, public or State interests or public organization renders the crime committed under sub-article (1) of this Article of particular gravity, the punishment shall be rigorous imprisonment from seven years to fifteen years and fine not less than Birr ten thousand and not exceeding Birr two hundred thousand.

፫/በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ሁለቱ ወይም ከዚያ በላይ ተደራርበው ሲገኙ ቅጣቱ ከአስር ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት የሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከሃያ ሺህ ብር እስከ አራት መቶ ሺህ ብር የሚደርስ መቀጮ ይሆናል።

፬/የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ጥቅም የማግኘት ወይም የማስገኘት ሐሳብ ሳይኖረው፦

ሀ) እራሱ ወይም የቅርብ ዘመዱ ባለጥቅም ወይም ባለአክሲዮን በሆነበት ድርጅት ወይም መስራች ወይም አባል በሆነበት የበጎ አድራጎት ድርጅት እና እርሱ በሚሠራበት መሥሪያ ቤት ወይም ድርጅት መካከል በንግድ ወይም በሌላ ሥራ፣ በግዢ ወይም በሽያጭ ወይም ከሚያከናውነው ሥራ ጋር በተያያዘ በማናቸውም የሥራ ግንኙነት ውል እንዲፈፀም ያደረገ እንደሆነ፤ ወይም

ለ) የተወሰኑ ንብረቶችን እንዳይገዛ ወይም እንዳይጫረት በህግ፣ በደንብ ወይም በመመሪያ ተከልክሎ እያለ በስሙ ወይም በሌላ ሰው ስም ወይም ከሌላ ሰው ጋር ንብረት የገዛ ወይም የተጫረተ እንደሆነ፣ በቀላል እስራት እና በመቀጮ ወይም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

፭/ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) አፈፃፀም "ዘመድ" ማለት አግባብ ባለው ህግ መሠረት ከተጠርጣሪው ጋር የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው ሰው ነው።

፮/በማንኛውም ደረጃ የሚገኝ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት የሥራ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ሆን ብሎ የሚስጥር ኮድ በሚጠቀሙ አሠራሮች የሚስጥር ኮዱን ማወቅ የማይገባው ሰው እንዲያውቀው፣ ወይም አንድ ሰው ብቻ ሊይዘው የሚገባውን ቁልፍ መያዝ የማይገባው ሰው እንዲይዘው በማድረግ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሀብት ወይም ንብረት እንዲመዘበር፣ እንዲወሰድ፣ ወይም እንዲጠፋ ያደረገ እንደሆነ፣ ከአሥር ዓመት እስከ ሃያ



3/ Where two or more of the circumstances mentioned in sub-article (2) of this Article are present concurrently, the punishment shall be rigorous imprisonment from ten years to twenty-five years and fine not less than Birr twenty thousand and not exceeding Birr four hundred thousand.

4/ Where a public servant or employee of a public organization, without having intent to obtain an advantage for himself or to procure the same for another:

a) has caused a contract to be concluded, relating to a business or other undertaking, a purchase or sale, or any transaction related to his function, between his office and an organization in which he himself or his close relative is an interested party or a shareholder, or with a charitable organization of which he is a founder or a member; or

b) has purchased certain property or taken part in an auction, while prohibited by law or regulations or directives from so doing, in his own name or in the name of other, or together with, another person; he shall be punishable with simple imprisonment and fine or rigorous imprisonment not exceeding five years and fine not exceeding Birr fifty thousand.

5/ For the application of sub-article (4) of this Article "relative" means a person who is related to the suspect, in accordance with the relevant law, by consanguinity or by affinity.

6/ Where any public servant or employee of public organization having the rank of officer or employee intentionally divulges any confidential information password or key of a safe the access of which is not allowed for other persons or gives such password or key of the safe destined to be held under one person's possession to another unauthorized person and such information disclosure results in the embezzlement or loss of public interest or public organization advantage, he

ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከሃምሳ ሺ.ህ ብር እስከ ሦስት መቶ ሺ.ህ ብር በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) የተመለከተው ወንጀል የተፈፀመው በቸልተኝነት የሆነ እንደሆነ ከሦስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከአሥር ሺ.ህ ብር እስከ ሃምሳ ሺ.ህ ብር በሚደርስ መቀጮ ያስቀጣል።

፰/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) አፈፃፀም ተጠርጣሪው የሚስጥር ኮዱ ወይም ቁልፉ ከእርሱ ፈቃድ ወይም ዕውቅና ውጭ የተወሰደ መሆኑን ካላስረዳ በስተቀር የሚስጥር ኮዱን ወይም ቁልፉን ሆነ ብሎ እንደሰጠ ይገመታል።

፱/ ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ አግባብ ባለው ኃላፊ እንዲጠቀምበት ወይም እንዲይዘው ያልተፈቀደ ለትን ወይም ያልተሰጠውን የሚስጥር ኮድወይም ቁልፍ ወስዶ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሀብት ወይም ንብረት የመዘበረ፣ የወሰደ ወይም ያጠፋ ወይም እንዲመዘበር፣ እንዲወሰድ ወይም እንዲጠፋ ያደረገ እንደሆነ፣ እንደነገሩ ሁኔታ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) ወይም (፯) መሠረት ይቀጣል።

## ፲፬. አደራ በተሰጠው ዕቃ ያለአግባብ ማዘዝ

፩/ ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ በሕግ አግባብ ሳይፈቀድለትና የግል ንብረት ለማድረግ በማሰብ ሳይሆን ታሽጎ የተረከበውን ጥቅል፣ ኢንቨሎፕ፣ ሰነድ፣ ባለዋጋ ነገር ወይም አደራ ወይም እንዲታሽግ የተረከበውን ማናቸውንም ዕቃ፦

ሀ) የከፈተ፣ ያስከፈተ፣ የወሰደ ወይም ያስወሰደ ወይም የእሽጉን ይዘት የገለጠ ወይም ዕቃውን አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፤ ወይም

ለ) የተገለገለበት ወይም ሌላ ሰው እንዲገለገል በት የፈቀደ እንደሆነ ፤

ከሰባት ሺ.ህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ይቀጣል።

shall be punishable with rigorous imprisonment from ten years to twenty years and fine not less than Birr fifty thousand and not exceeding Birr three hundred thousand.

7/ Where the crime specified in sub-article (6) of this Article is committed negligently, the punishment shall be rigorous imprisonment from three years to seven years and fine not less than Birr ten thousand and not exceeding Birr fifty thousand.

8/ For the application of sub-article (6) of this Article, unless the suspect proves satisfactorily that the password or key of the safe is taken without his permission or knowledge, it shall be presumed that he disclosed such information or handed over the key intentionally.

9/ Any public servant or employee of public organization that uses or takes password or key of safe he is not authorized to use or take and as a result public property or public organization advantage is embezzled or lost by him or being cause of embezzlement shall, depending up on the circumstance, be punishable in accordance with sub-article (6) or (7) of this Article.

## 14. Unlawful Disposal of Object in Charge

1/ Any public servant or employee of a public organization who, takes a parcel, envelope, document, valuable material or any other object whatsoever received on deposit or under seal; without lawful authority and without intent to appropriate:

a) opens or permits to be opened, takes or permits to be taken, communicates or hands over to another;or

b) makes use of such objects, or authorizes another to make use of them;

Shall be punishable with fine not exceeding seven thousand Birr or simple imprisonment not exceeding five years.

፪/ ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ለራሱ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን ወንጀል የፈፀመ እንደሆነ፣ እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት እና ከሦስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ፣ ወይም ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከሃያ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

፫/ የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት ወይም የጥፋተኛው የኃላፊነት ወይም የሥልጣን ደረጃ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የተፈጸመውን ወንጀል ከባድ አድርጎት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ፅኑ እስራት እና ከአምስት ሺህ ብር በማያንስ ከስልሳ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይሆናል።

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ወንጀል የተፈፀመው በቸልተኝነት እንደሆነ፣ ቅጣቱ እስከ ሁለት ሺህ ብር የሚደርስ መቀጮ ይሆናል።

## ፲፭. በሥራ ተግባር የሚፈፀም የመውሰድና የመሰወር ወንጀል

፩/ የማይገባ ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ ማንኛውም፦

ሀ) የመንግስት ሠራተኛ በብርበራ፣ በመያዝ፣ በመውረስ ሥርዓት፣ በሐራጅ ሽያጭ፣ በሕግ ውርስ ወይም ፍርዱ በንብረቱ ላይ እንዲፈፀም በመወሰኑ ወይም ይህን የመሰለ ማናቸውም ሥራ በሚያከናውንበት ወይም በሚያስፈፅምበት ጊዜ፤ ወይም

ለ) የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በማንኛውም የሥራ አጋጣሚ በእጁ ሊገቡ የቻሉትን ወይም በአደራ የተረከባቸውን ወይም የሚጠብቃቸውን፣

ዕቃዎችን፣ ሰነዶችን፣ ባለዋጋ ነገሮችን፣ ጥሬ ገንዘቦችን፣ ተንቀሳቃሽ ወይም አላቂ ዕቃዎችን የወሰደ ወይም የሰወረ እንደሆነ፤ እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት እና ከሦስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ

2/ Where a public servant or employee of a public organization commits the offence prescribed under sub-article (1) of this Article in order to solicit an advantage to himself, in accordance to the circumstances of the case, the punishment shall be simple imprisonment not less than one year and fine not exceeding Birr three thousand or rigorous imprisonment not exceeding seven years and fine not exceeding Birr twenty thousand.

3/ Where, the extent of the advantage received the degree of responsibility or power of the culprit or renders the crime committed under sub-article (2) of this Article of particular gravity, the punishment shall be rigorous imprisonment from five years to fifteen years, and fine not less than five thousand Birr and not exceeding sixty thousand Birr.

4/ Where the crime specified under sub-article (1) of this Article is committed negligently, the punishment shall be fine not exceeding two thousand Birr.

## 15. Appropriation and Misappropriation in the Discharge of Duties

1/ If, with intent to obtain for himself or to procure for another an undue material advantage:

a) any public servant in the course of a search, seizure or process of confiscation, public auction, sequestration or distrait, or during any other similar procedure; or

b) any public servant or employee of a public organization who by any means have the opportunity to control things which have come into his hands by virtue of or in the course of his duties or which have been entrusted to him or are under his control;

appropriates objects, legal instruments, securities, cash, chattels or any consumable thing whatsoever, he shall be punishable, according to the circumstances of the case,

ወይም ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከአሥር ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

፪/ የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት፣ የጥፋተኛው የኃላፊነት ወይም የሥልጣን ደረጃ ወይም በግለሰብ፣ በህዝብ፣ በመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ጥቅም ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛነት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተፈጸመውን ወንጀል ከባድ አድርጎት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከሰባት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ፅኑ እስራት እና ከሰባት ሺህ ብር በማያንስ ከስልሳ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይሆናል።

፫/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፪) ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ሁለቱ ወይም ከዚያ በላይ ተደራርበው ሲገኙ ቅጣቱ ከአስር ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት የሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከአሥር ሺህ ብር የማያንስ እና ከአንድ መቶ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል።

## ፲፮.በሥልጣን ወይም በኃላፊነት መነገድ

፩/ ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በሥራው ምክንያት ባለው ወይም አስመስሎ ባቀረበው ተሰሚነት፦

ሀ) አግባብ ባለው ባለስልጣን ወይም ኃላፊ ተወስኖ የሚሰጥ የሥራ ደረጃ፣ ሹመት፣ ሥራ፣ ሽልማት፣ የአገልግሎት ዋጋ፣ ልዩ ችሮታ፤

ለ) በቁጥጥሩ ወይም በአመራሩ ሥር በሚገኙ ባለስልጣኖች፣ኃላፊዎች ወይም የአስተዳደር ክፍሎች የሚደረግ ውል፣ የንግድ ስምምነት፣ የሥራ ጨረታ፣ የዕቃ ማቅረብ ውል፣ ወይም ሌላ ጥቅም፤ ወይም

ሐ) በአጠቃላይ ከአንድ ባለስልጣን፣ ኃላፊ ወይም የአስተዳደር ክፍል የሚሰጠውን ጥቅም ወይም የሚረዳ ውሳኔ፤

with simple imprisonment for not less than one year and fine not less than Birr three thousand or with rigorous imprisonment not exceeding ten years and fine not exceeding Birr ten thousand.

2/ Where the extent of advantage obtained, the degree of power or responsibility of the culprit or the extent of the harm to private, public or State interest or advantage of public organization renders the crime committed under sub-article (1) of this Article of particular gravity, the punishment shall be rigorous imprisonment from seven years to fifteen years and fine not less than seven thousand Birr and not exceeding sixty thousand Birr.

3/ Where two or more of the circumstances mentioned under sub-article (2) of this Article are present concurrently, the punishment shall be rigorous imprisonment from ten years to twenty-five years and fine not less than Birr ten thousand and not exceeding Birr hundred thousand.

## 16. Traffic in Official Power or Responsibility

1/ Any public servant or employee of a public organization who solicits or accepts a gift or other advantage to procure for another person, through the exercise of the influence, real or pretended, he enjoys by reason of his being a public servant or employee of a public organization:

a) promotion, appointment, employment, reward, remuneration or favor within the dispensation of the competent authority;

b) contracts, deals, undertakings, orders,tenders or other advantage resulting from agreements concluded with the public authorities or with an administration placed under his control or direction; or

c) in general, an advantage or a favorable decision on the part of a public authority or administration;

ለሌላ ሰውለማስገኘት ስጦታ ወይም ሌላ ጥቅም የጠየቀ ወይም የተቀበለ እንደሆነ፣ እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከሦስት ሺህ ብር በማያንስ ከስልሳ ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

፪/ ኃላፊነቱ ወይም ግዴታው እንዲጣስ የተፈለገበት ዓላማ፣ የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት፣ የጥፋተኛው የኃላፊነት ወይም የሥልጣን ደረጃ ወይም በግለሰብ፣ በመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ጥቅም ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛነት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተፈጸመውን ወንጀል ከባድ አድርጎት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከሰባት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ፅኑ እስራት እና ከሰባት ሺህ ብር የማያንስ ከአንድ መቶ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል።

፫/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፪) ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ሁለቱ ወይም ከዚያ በላይ ተደራርበው ሲገኙ ቅጣቱ ከአስር ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት የሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከአሥር ሺህ ብር የማያንስ እና ከሁለት መቶ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል።

**፲፯. በህገወጥ መንገድ መሰብሰብ ወይም ማስረከብ**

፩/ ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት በማሰብ፦

ሀ) ሊከፈል የማይገባ መሆኑን ወይም በህግ ከተወሰነው ታሪፍ በላይ መሆኑን እያወቀ ቀረጥ፣ ግብር፣ ልዩ ልዩ ገቢ ወይም ልዩ ልዩ የገቢ ጥቅም፣ ምንዳ፣ ደመወዝ፣ ካሣ ወይም ሌላ ወጪ የሰበሰበ ወይም እንዲሰበሰብ ያዘዘ እንደሆነ፣

ለ) ማናቸውም ዕቃ ወይም ክፍያ በሚያስረክብበት ወይም በሚሰጥበት ጊዜ ማስረከብ ወይም መክፈል ከሚገባው አሳንሶ ያስረከበ ወይም የከፈለ እንደሆነ፣

እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት እና ከሦስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከአሥር ሺህ ብር በማያንስ ከሠላሳ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

shall be punishable, according to the circumstances of the case, from one year to ten year rigorous imprisonment and fine not less than Birr three thousand and not exceeding Birr sixty thousand.

2/ Where the purpose of the breach of responsibility or duty solicited, the extent of the advantage received, the degree of power or responsibility of the culprit or the extent of the harm to private, public or State interests or advantage of public organization renders the crime committed under sub-article (1) of this Article of particular gravity, the punishment shall be rigorous imprisonment from seven years to fifteen years and fine not less than Birr seven thousand and not exceeding Birr one hundred thousand.

3/ Where two or more of the circumstances mentioned in sub-article (2) of this Article are present concurrently, the punishment shall be rigorous imprisonment from ten years to twenty-five years and fine not less than Birr ten thousand and not exceeding Birr two hundred thousand.

**17. Illegal Collection or Disbursement**

1/ Any public servant or employee of a public organization who, with intent to obtain an undue advantage for himself:

a) collects or orders the collection of taxes, dues, miscellaneous revenues or incomes, wages, salaries, compensation or other expenses, which he knows not to be due or to be in excess of what is legally due; or

b) hands over or pays less than is due, while consigning or disbursing any object or money;

shall be punishable, according to the circumstances of the case, with simple imprisonment for not less than one year, and a fine not exceeding Birr three thousand or with rigorous imprisonment not exceeding ten years and fine not less than ten thousand Birr and not exceeding thirty thousand Birr.

፪/ ኃላፊነቱ ወይም ግዴታው እንዲጣስ የተፈለገበት ዓላማ፣ የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት፣ የጥፋተኛው የኃላፊነት ወይም የሥልጣን ደረጃ ወይም በግለሰብ፣ በመንግስት፣ ወይም በህዝባዊ ድርጅት ጥቅም ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛነት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተፈጸመውን ወንጀል ከባድ አድርጎት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከሰባት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ፅኑ እስራት እና ከሰባት ሺህ ብር በማያንስ እና ከስልሳ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይሆናል።

፫/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፪) ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ሁለቱ ወይም ከዚያ በላይ ተደራርበው ሲገኙ ቅጣቱ ከአስር ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት የሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከአሥር ሺህ ብር የማያንስ እና ከአንድ መቶ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል።

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ወንጀል የተፈፀመው በቸልተኝነት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ቀላል እስራት እና መቀጮ ይሆናል።

## ፲፰. ያላግባብ ጉዳይን ማጓተት

ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራው ምክንያት በቀረበለት ጉዳይ ላይ ጥቅም ካለው ማንኛውም ሰው በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ጥቅም ለማግኘት፣ በጉዳዩ ላይ ጥቅም ያለውን ማንኛውንም ወገን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት ሲል ከሕግ፣ ከሥራ ደንብ፣ ወይም ከመመሪያ ወይም ከተለመደው አሠራር ውጭ ያለ በቂ ምክንያት ያልወሰነ፣ ያዘገየ ወይም ባለጉዳይን ያጉላላ እንደሆነ፣ እንደነገሩ ሁኔታ በመቀጮ ወይም በቀላል እስራት ወይም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

## ፲፱. ዋጋ ያለውን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማግኘት

፩/ ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ምክንያት ሳይኖረው ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማናቸውም ዋጋ ያለውን ነገር የተቀበለ እንደሆነ፣ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

2/ Where the purpose of the breach of responsibility or duty solicited, the extent of the advantage received, the degree of power or responsibility of the culprit or the extent of the harm to private, public or State interests renders the crime committed under sub-article (1) of this Article of particular gravity, the punishment shall be rigorous imprisonment from seven years to fifteen years and fine not less than Birr seven thousand and not exceeding Birr sixty thousand.

3/ Where two or more of the circumstances mentioned in sub-article (2) of this Article are present concurrently, the punishment shall be rigorous imprisonment from ten years to twenty five years and fine not less than Birr ten thousand and not exceeding Birr one hundred thousand.

4/ Where the crime specified under sub-article (1) of this Article is committed negligently, it shall be punishable with simple imprisonment and fine.

## 18. Undue Delay of Matters

Any Public servant or employee of a public organization who, with intent to obtain an advantage, directly or indirectly, from any person interested in a matter brought to his attention, by reason of his responsibility or duty; or to benefit or injure any party interested in such matter, fails, without good cause, to decide on or delays the matter or abuses the interested party contrary to law, manuals or directives or accepted office practices, shall be punishable, according to the circumstances of the case, with fine or simple imprisonment, or with rigorous imprisonment not exceeding five years and fine not exceeding five thousand Birr.

## 19. Taking Things of Value Without or With Inadequate Consideration

1/ Any public servant or employee of a public organization, who, without proper cause, receives a thing of value without payment or with inadequate payment; shall be punishable with simple imprisonment not exceeding five years and fine not exceeding Birr five thousand.

፪/ ንብረትን፣ የፋይናንስ አቋምን ወይም ስጦታ መቀበልን ማስመዝገብ ወይም ማሳወቅ እንደሚገባ በህግ ወይም በደንብ በተደነገገ ጊዜ አለማሳወቅ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው መሰረት ያስቀጣል።

፫/ በአገሩ ወይም በአካባቢው ባህል ወይም ልማድ መሰረት እንደተራ የወዳጅነት ምልክት የሚሰጥ ዋጋ ያለው ስጦታ መቀበል ወይም ከስጋ ወይም ከጋብቻ የቅርብ ዘመድ ወይም የቅርብ ወዳጅ ስጦታ ማግኘት በዚህ አንቀጽ ለተመለከተው ወንጀል ማቋቋሚያ አይሆንም።

## ፳. ያለአግባብ ፍቃድ መስጠት ወይም ማፅደቅ

፩/ ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ ሆን ብሎ ብቁ ላልሆነ ወይም በህግ ሊሰጠው ለማይገባ ሰው ማናቸውንም የንግድ ወይም የሥራ ፈቃድ የሰጠ ወይም ያፀደቀ እንደሆነ፣ ወይም አንድ ነገር የሚከናወንበትን ቦታ ያለ አግባብ የፈቀደ ወይም የሰጠ እንደሆነ፣ እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እስራትና መቀጮ ወይም ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከሦስት ሺ.ህ ብር በማያንስ ከሠላሳ ሺ.ህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

፪/ ማንኛውም ፈቃድ ወይም ማረጋገጫ የመስጠት ኃላፊነት ያለው ሰው ሆን ብሎ ብቁ ላልሆነ ወይም በህግ ሊሰጠው ለማይገባ ሰው የመንጃ ፈቃድ፣ የተሽከርካሪ የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ፣ የሰው የጤንነት ማረጋገጫ ወይም የትምህርት ደረጃ ማረጋገጫ የሰጠ ወይም ያፀደቀ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ይቀጣል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) የተመለከተው ወንጀል የተፈጸመው በቸልተኝነት እንደሆነ ቅጣቱ ቀላል እስራትና መቀጮ ይሆናል።

## ፳፩. ምንጩ ያልታወቀ ንብረት እና ገንዘብ

፩/ ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የሆነ ወይም የነበረ ሰው፦

2/ Where the declaration or registration of property, financial status or gifts received, is required by law or regulations, failure to do so shall be punishable as prescribed under sub-article (1) of this Article.

3/ Receiving a valuable gift considered by national or local culture or custom as a common manifestation of affection, or obtaining a gift from a close relative by consanguinity or affinity or from a close friend, shall not constitute a crime under this Article.

## 20. Granting or Approving License Improperly

1/ Any public servant who intentionally grants or approves a business license or work permit to an ineligible person or to a person not legally entitled to obtain such license or permit, or improperly grants or permits a place where things are to be done, shall be punishable, according to the circumstances of the case, with simple imprisonment and fine or with rigorous imprisonment not exceeding ten years and fine not less than three thousand Birr and not exceeding thirty thousand Birr.

2/ Any person who has the power to issue licence or certificate, intentionally grants or approves a driving license, certificate of road worthiness of a vehicle, certificate of health of a person or a certificate of educational qualification to an ineligible person or to a person not legally entitled to obtain such license or certificate, he shall be punishable as prescribed under sub-article (1) of this Article.

3/ Where the crime specified under sub-article (1) or (2) of this Article is committed negligently, the punishment shall be simple imprisonment and fine.

## 21. Possession of Unexplained Property

1/ Any public servant or employee of a public organization, being or had been in office, who:

ሀ) የኑሮ ደረጃው አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚያገኘው ወይም ሲያገኘው ከነበረው ህጋዊ ገቢ የበለጠ እንደሆነ፤

ለ) ያለው ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚያገኘው ወይም ሲያገኘው ከነበረው ህጋዊ ገቢ ጋር የማይመጣጠን እንደሆነ፤

የዚህ ዓይነቱ የኑሮ ደረጃ እንዴት ሊኖረው እንደቻለ ወይም ያለው ንብረት ወይም ገንዘብ በእጁ እንዴት ሊገባ እንደቻለ ለፍርድ ቤት ካላስረዳ በስተቀር የንብረቱ ወይም የገንዘብ ምንጩ መወረስ ወይም ለባለቤቱ መመለስ እንደተጠበቀ ሆኖ በቀላል እስራት እና በመቀጮ፤ ወይም ነገሩ ከባድ ሲሆን ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከአምስት ሺ.ህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ለ) የተጠቀሰው ወንጀል በፍርድ ቤት እየታዩ ባለበት ጊዜ ማንኛውም ሰው ከተከሳሽ ጋር ካለው ቅርበት ወይም ሌሎች ሁኔታዎች የተነሳ ለተከሳሹ ባለአደራ በመሆን አንድን ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ እንደያዘ ወይም ከተከሳሹ በስጦታ እንዳገኘ ፍርድ ቤት ካመነበት ጉዳዩን በሌላ ማስረጃ ካላፈረሰ በስተቀር ንብረቱ ወይም የገንዘብ ምንጩ በተከሳሹ ይዞታ ሥር እንደሆነ ይቆጠራል።

## ፳፪. የሥራ ሚስጥርን መግለጽ

፩/ አግባብነት ባለው ህግ አያስጠይቅም ተብሎ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት፣ ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ በሥራው ምክንያት ያወቀው ሆኖ በጠባዩ ሚስጥር የሆነውን ወይም በሚስጥር እንዲጠበቅ የታዘዘውን ወይም ለህዝብ እንዳይገለፅ የተከለከለውን መረጃ፣ ሰነድ ወይም ፍሬ ነገር ሥራውን ወይም ሹመቱን ከለቀቀ በኋላ ቢሆንም እንኳ የገለፀ ወይም ያስተላለፈ እንደሆነ ከሁለት

a) maintains a standard of living above that which is commensurate with the official income from his present or past occupation or other means; or

b) is in control of pecuniary resources or property disproportionate to the official income from his present or past occupation or other means;

unless he proves satisfactorily before the Court of law as to how he was able to maintain such a standard of living or how such pecuniary resources or property came under his control, shall be punishable, without prejudice to the confiscation of the property or the restitution to the third party, with simple imprisonment and fine, or in serious cases, with rigorous imprisonment not exceeding five years and fine not exceeding Birr five thousand.

2/ Where the Court, during proceeding under paragraph (b) sub-article (1) of this Article is satisfied that there is reason to believe that any person, owing to his closeness to the accused or other circumstances, was holding pecuniary resource or property in trust for or otherwise on behalf of the accused, such resources, or property shall, in the absence of evidence to the contrary, be presumed to have been under the control of the accused.

## 22. Breaches of Official Secrecy

1/ Without prejudice to the exemptions prescribed in relevant laws, any public servant or employee of public organization who discloses or communicates information, document or fact which is secret by its nature, or have been secret by order, or is not intended for publication which has come to his knowledge in the course of his duties, even where his occupation or position has been ended, shall be punishable with rigorous imprisonment not less than two years and not exceeding twelve years and fine not less than Birr five thousand and not exceeding Birr thirty thousand.

ዓመት በማያንስ ከአስራ ሁለት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከአምስት ሺህ ብር እስከ ከሠላሳ አምስት ሺህ ብር በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለተፈጸመው ወንጀል ጥፋተኛው የተለየ ሚስጥር የመጠበቅ ግዴታ ወይም እምነት የተጣለበት ወይም ወንጀሉ በተለይ ከፍ ያለ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት የሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከአሥር ሺህ ብር እስከ ሃምሳ ሺህ ብር የሚደርስ መቀጮ ይሆናል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ወንጀል የተፈፀመው በቸልተኝነት ሲሆን ከአንድ ዓመት ያልበለጠ ቀላል እስራት እና በመቀጮ ይቀጣል፤ ሆኖም የወንጀሉ አፈጻጸም በንዑስ አንቀጽ (፪) እንደተመለከተው ከባድ ሲሆን ከሦስት ዓመት ያልበለጠ ቀላል እስራት እና ከአምስት ሺህ ብር ያልበለጠ መቀጮ ይሆናል፡፡

**፳፫. <u>መንግስታዊ ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት፣ ወደ ሀሰት መለወጥ ወይም በሐሰተኛ ሰነድ መገልገል</u>**

፩/ ማንኛውም ሰው የሌላውን ሰው መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ማናቸውም መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ፦

ሀ) አንድ ፅሑፍ፣ መዝገብ ወይም ማንኛውንም ሰነድ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት በማስመሰል ያዘጋጀ ወይም የፈጠረ እንደሆነ፤

ለ) በመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት መዝገብ፣ ጽሑፍ ወይም ሰነድ የሰፈረን እውነተኛውን ጽሑፍ በመለወጥ ወይም በመደለዝ፣ በሐሰተኛ ፊርማ፣ በእጅ በተደረገ ምልክት ወይም በጣት ፊርማ፣ በማህተም ወይም የሌለውን ስልጣን ወይም ችሎታ እንዳለው አስመስሎ በመፈረም ሐሰተኛ ሰነድ የፈጠረ እንደሆነ፤ ወይም

2/ Where the crime committed under sub-article (1) of this Article is aggravated due to the criminal's special obligation to maintain secrecy or special position of trust, or to the gravity of the damage caused by the breach of duty, the punishment shall be rigorous imprisonment not less than five years and not exceeding twenty years and fine not less than Birr ten thousand and not exceeding Birr fifty thousand.

3/ Where the crime specified under sub-article (1) of this Article is committed negligently, the punishment shall be fine or simple imprisonment not exceeding one year or, in the case of the crime under sub-article (2) of this Article being grave, the punishment shall be simple imprisonment not exceeding three years and fine not exceeding Birr five thousand.

**23. <u>Material Forgery of Official or Public Organization Documents</u> or Using Forged Document**

1/ Whosoever with intent to injure the rights or interests of another, or to obtain for himself or to procure for another any undue right or advantage:

a) falsely executes or prepares an instrument, document or any writing of a public office or public organization; or

b) counterfeits a document, a file or any other written instrument of a public office or public organization, especially by changing his handwriting, by affixing to the instrument a false signature, mark or stamp, or by signing it in a false capacity purporting to certify its authorship; or

ሐ) አንድን የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰነድ በተለይም የፈራሚውን ስም ወይም ፊርማ ወይም የሰነዱን ይዘት፣ አሃዝ፣ ፍሬ ነገር ወይም ዝርዝር መግለጫ በሙሉ ወይም በከፊል በመለወጥ፣ በማሻሻል፣ በመቀነስ ወይም በመጨመር ወይም በማጥፋት ወደ ሐሰተኛነት የለወጠ ወይም ማናቸውንም ሐሰተኛ ፍሬ ነገር ያስገባ ወይም እንዲገባ ያደረገ እንደሆነ፣

ከሦስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከሦስት ሺህ ብር እስከ ሰላሳ ሺህ ብር በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ወንጀል የተፈጸመው እነዚህን የመሳሰሉትን መዝገቦች፣ ጽሑፎች፣ የታወቁ ሰነዶች ወይም ሌሎች ሰነዶችን እንዲያዘጋጅ፣ እንዲመዘግብ፣ እንዲጠብቅ ወይም ከነዚሁ ውስጥ ቅጅዎችን እንዲሰጥ ኃላፊነት በተሰጠው የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ እንደሆነ ወይም ሰነዱን በመገልገል የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት ወይም በግለሰብ፣ በመንግስት፣ ወይም በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝብ ጥቅም ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛነት፦

ሀ) የወንጀሉን አፈጻፀም ከባድ አድርጎት እንደሆነ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት የሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከአምስት ሺህ ብር እስከ ሃያ አምስት ሺህ ብር የሚደርስ መቀጮ ይሆናል፤

ለ) የወንጀሉ አፈጻፀም በጣም ከባድ አድርጎት እንደሆነ ቅጣቱ እስከ ዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት ድረስ ይሆናል።

፫/ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው መሰረት ወደ ሐሰት በተለወጠ ወይም በሐሰት በተዘጋጀ ሰነድ እያወቀ የተገለገለበት እንደሆነ በዚሁ ንዑስ አንቀጽ በተመለከተው ቅጣት ይቀጣል።

፬/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በስሙ ወይም ለራሱ ጥቅም እንዲውል ተመሳስሎ የተሠራ ወይም ወደ ሐሰት የተለወጠ ሰነድ በቤቱ፣

c) falsifies an instrument of a public office or public organizations especially by altering, modifying, adding or removing, or deleting, in whole or in part, the name or signature of its author or the terms, figure, facts or material details it contains;

shall be punishable with rigorous imprisonment not less than three years and not exceeding ten years and fine not less than Birr three thousand and not exceeding Birr thirty thousand.

2/ Where the crime specified in sub article (1) of this article is committed by a public servant or employee of public organization officially entrusted with the drawing up, filing, keeping or delivery of extracts from the registers, instruments, deeds or documents in question, or when the advantage obtained or the damage caused to individual, state, public organization or public interest being high renders the crime of:

a) particular gravity, the punishment shall be rigorous imprisonment from five years to twenty five years and fine not less than Birr five thousand and not exceeding Birr twenty five thousand; or

b) serious gravity, the punishment shall extend up to life imprisonment.

3/ Whosoever, knowingly uses documents mentioned under sub-article (1) of this Article shall be punishable under same sub-article.

4/ For the application of this article unless proved otherwise any public servant or employee of a public organization shall be presumed that he produced or caused the production of the document where the

በተሽከርካሪው፣ በኪሱ ወይም በማንኛውም አግባብ በቁጥጥሩ ሥር የተገኘ እንደሆነ ተቃራኒ ማስረጃ ካላቀረበ በስተቀር ሰነዱን እራሱ እንዳዘጋጀው ወይም እንዲዘጋጅ እንዳደረገው ይገመታል።

## ፳፬.መንግስታዊ ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰነዶችን ማጥፋት ወይም ጉዳት ማድረስ

፩/ ማንኛውም ሰው የሌላውን ሰው መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ማናቸውንም መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ በመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝብ ሰነድ ላይ ጉዳት እንዲደርስበት ያደረገ፣ የቀደደ፣ ያጠፋ፣ ጥቅም ላይ እንዳይውል ያደረገ ወይም የወሰደ እንደሆነ ከሦስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከአሥር ሺህ ብር እስከ ሰባ ሺህ ብር በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ወንጀል የተፈፀመው እንደዚህ ያለውን ሰነድ እንዲያዘጋጅ፣ እንዲመዘግብ፣ እንዲጠብቅ ወይም እንዲሰጥ ኃላፊነት በተሰጠው የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከሰባት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት የሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከሃያ አምስት ሺህ ብር እስከ አንድ መቶ ሺህ ብር የሚደርስ መቀጮ ይሆናል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተው ወንጀል አፈፃፀም በጣም ከባድ በሆነ ጊዜ ቅጣቱ ዕድሜ ልክ እስራት ይሆናል።

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) የተመለከተው ወንጀል የተፈፀመው በቸልተኝነት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት ያልበለጠ ቀላል እስራት እና ከሰባት ሺህ ብር ያልበለጠ መቀጮ ይሆናል።

document falsified or counterfeited in his name or for his advantage is found in his residence, vehicle, pocket or in any manner under his control.

## 24. Suppression of Official or Organizational Documents

1/ Whosoever, with intent to injure the rights or interests of another, or to obtain for himself or to procure for another any undue right or advantage damages, tears, destroys, suppresses or takes an instrument belonging to a public office or a public organization shall be punishable with rigorous imprisonment not less than three years and not exceeding ten years and fine not less than Birr ten thousand and not exceeding Birr seventy thousand.

2/ Where the crime specified under sub-article (1) of this Article is committed by a public servant or employee of a public organization officially entrusted with the drawing up registration, keeping, disposal or delivery of such instrument, the punishment shall be rigorous imprisonment not less than seven years and not exceeding twenty-five years and fine not less than Birr twenty five thousand and not exceeding Birr one hundred thousand.

3/ Where the crime specified under sub-article (2) of this Article is very serious, the punishment shall extend up to life imprisonment.

4/ Where the crime specified under sub-articles (1) or (2) of this Article is committed negligently, the punishment shall be simple imprisonment not exceeding five years and fine not exceeding Birr seven thousand.

## ፳፭.ጉቦ ወይም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም መስጠት

፩/ ማንኛውም ሰው አንድ የመንግስት ሠራተኛ ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራ ግዴታው ማድረግ የማይገባውን እንዲያደርግ ወይም ማድረግ የሚገባውን እንዳያደርግ ጥቅም ወይም ስጦታ የሰጠ ወይም ያቀረበ እንደሆነ፣ እንደ ነገሩ ሁኔታ በቀላል እስራት እና በመቀጮ፣ ወይም ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከሰባት ሺህ ብር በማያንስ ከሠላሳ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

፪/ ማንኛውም ሰው ከዓለም አቀፍ ግብይት ወይም ግንኙነት ጋር በተያያዘ ለማንኛውም የሌላ አገር መንግስት፣ ድርጅት ወይም የዓለም አቀፍ ድርጅት ባለስልጣን ወይም ሠራተኛ በሥራ ግዴታው ማድረግ የማይገባውን እንዲያደርግ ወይም ማድረግ የሚገባውን እንዳያደርግ ጥቅም ወይም ስጦታ የሰጠ ወይም ያቀረበ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው መሠረት ይቀጣል።

፫/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፲፪ ለተመለከቱት ሰዎች ጉቦ የሰጠ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው መሠረት ይቀጣል።

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፪) ወይም (፫) ለተመለከተው ወንጀል ወንጀል አድራጊው ያቀረበው ገንዘብ ከፍተኛነት፣ ወይም ድርጊቱ በግለሰብ፣ በህዝብ፣ በመንግስት፣ ወይም በህዝባዊ ድርጅት ጥቅም ላይ ከፍተኛ ጉዳትን በማስከተሉ የወንጀሉን አፈጻፀም ከባድ አድርጎት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ፅኑ እስራት እና ከአምስት ሺህ ብር የማያንስ ከአንድ መቶ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል።

፭/ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት ማድረግ የሚገባውን ተግባር እንዲያከናውን ሲል ይህንኑ ተግባር ከመፈፀሙ በፊት ወይም ከፈፀመ በኋላ ለዚሁ ሠራተኛ ጥቅም ወይም ስጦታ የሰጠ ወይም ያቀረበ ማንኛውም ሰው፤ እንደ ነገሩ ሁኔታ በመቀጮ፣ በቀላል እስራት እና በመቀጮ፣ ወይም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

## 25. Giving Bribe or Undue Advantage

1/ Whosoever, with intent to procure a public servant or employee of a public organization to perform or omit an act in violation of the duty proper to his office, gives or offers an advantage or gift to such public servant or employee of a public organization, shall be punishable, according to the circumstances of the case, with simple imprisonment and fine, or with rigorous imprisonment not exceeding seven years and fine not less than Birr seven thousand and not exceeding Birr thirty thousand.

2/ Whosoever, gives or offers an advantage or gift to any official or employee of a foreign State or international organization, with intent to procure him to perform or omit an act related to international trade or transaction in violation of his official duties shall be punishable as provided under sub-article (1) of this Article.

3/ Whosoever offers bribe to the individuals mentioned under Article 12 of this Proclamation shall be punishable as provided under sub-article (1) of this Article.

4/ Where the purpose of the breach of responsibility or duty solicited, the extent of the advantage offered or promised, the degree powers or responsibility of the culprit or the extent of the harm to private, public or State interests or public organizations renders the crime committed under sub-articles (1), (2) or (3) of this Article of particular gravity, the punishment shall be rigorous imprisonment from five years to fifteen years and fine not less than Birr five thousand and not exceeding Birr one hundred thousand.

5/ Any person who, in consideration for the performance by a public servant or employee of a public organization of an act proper to his office, gives or offers him an advantage or a gift before or after the performance of such an act, shall be punishable, according to the circumstances of the case, with fine-or simple imprisonment and fine, or with rigorous imprisonment not exceeding five years and fine not exceeding Birr five thousand.

፮/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፭) የተመለከተው ወንጀል የተፈፀመው የሕግ ሰውነት በተሰጠው ሰው የሆነ እንደሆነ፣ በጥፋቱ ከሚሰጠው ቅጣት በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛው ከመንግስት መሥሪያ ቤት፣ ከመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም ከህዝባዊ ድርጅት ጋር ማናቸውንም ዓይነት ውል ወይም ግብይት እንዳይፈፅም በዘላቂነት ወይም ለተወሰነ ጊዜ የሚከለክል ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

## ፳፮. ዋጋ ያለውን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ መስጠት

፩/ ማንኛውም ሰው ተገቢ ምክንያት ሳይኖረው ለማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ወይም ከእርሱ ጋር ግንኙነት ላለው ማንኛውም ሌላ ሰው ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማናቸውንም ዋጋ ያለው ነገር ያቀረበ፣ የሰጠ ወይም ለመስጠት የተስማማ እንደሆነ፣ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

፪/ በአገሩ ወይም በአካባቢው ባህል ወይም ልማድ መሰረት እንደተራ የወዳጅነት ምልክት የሚሰጥ ዋጋ ያለው ስጦታ መስጠት ወይም ለስጋ ወይም ለጋብቻ የቅርብ ዘመድ ወይም ለቅርብ ወዳጅ ስጦታ መስጠት በዚህ አንቀጽ ለተመለከተው ወንጀል ማቋቋሚያ አይሆንም።

## ፳፯. ማቀባበል

ማንኛውም ሰው ለራሱ ማናቸውንም ዓይነት ጥቅም ባያገኝም እንኳ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራን ለሚያከናውን ሰው ጉቦ ለመስጠት ገንዘብ፣ ዋጋ ያለው ነገር፣ አገልግሎት ወይም ሌላ ዓይነት ጥቅም ከሌላ ሰው የተቀበለ እንደሆነ፣ ወይም የራሱን የባንክ ሂሳብ እንደዚህ ዓይነት ጉቦ ለማቀባበል ያዋለ እንደሆነ፣ ወይም ጉቦ እንዲሰጣጡ ሁኔታዎችን ያመቻቸ፣ ያገናኘ፣ ያስማማ ወይም የደለለ እንደሆነ፣ እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እስራት እና በመቀጮ፣ ወይም ከሦስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከሦስት ሺህ ብር እስከ አሥር ሺህ ብር በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።

6/ Where any one of the crimes specified from sub-articles (1) to (5) of this Article is committed by a juridical person, the court may, in addition to the punishment, give an order depriving the culprit, permanently or temporarily, of his right to take part in any trade or transaction with public office, public enterprise or public organization.

## 26. Giving Things of Value Without or With Inadequate Consideration

1/ Whosoever, without adequate reasons offers, gives or agrees to give to any public servant or employee of a public organization or to any other person related to him, anything of value without payment or with an inadequate payment shall be punishable with simple imprisonment not exceeding five years and fine not exceeding Birr five thousand.

2/ Giving or offering a valuable gift considered by national or local culture or custom as a common manifestation of affection or giving a gift to a close relative by consanguinity or affinity or to a close friend, does not constitute a crime under this Article.

## 27. Facilitating Act of Bribery

Whosoever, even without receiving any consideration for himself, accepts money, a valuable thing, a service or some other benefit from another with a view to giving it as bribe to a public servant or employee of a public organization or uses his banking account for such transaction or creates condition or mediates or offers meeting places for such bribery, shall be punishable, according to the circumstances of the case, with simple imprisonment and fine, or with rigorous imprisonment not less than three years and not exceeding ten years; and fine not less than Birr three thousand and not exceeding Birr ten thousand.

፳፰.በሌለው ስልጣን መጠቀም

ማንኛውም ሰው፦

፩/ ከመንግስት ወይም ከህዝባዊ ድርጅት ሥራው ከታገደ፣ ከተዛወረ፣ ከተሻረ ከተወገደ ወይም ሥልጣኑን ወይም ኃላፊነቱን ከተወ በኋላ በሥራው ላይ ያለ በማስመሰል፤

፪/ ለወደፊቱ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ እሆናለሁ ብሎ በማሳመን፤ ወይም

፫/ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ሳይሆን መስሎ በመቅረብ፤

ይህንን አደርጋለሁ በማለት የተስፋ ቃል በመግባት ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ወይም ስጦታ ከሌላ ሰው ላይ የጠየቀ ወይም የተቀበለ እንደሆነ፣ እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እስራት እና በመቀጮ፣ ወይም ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከአሥር ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

፳፱.በግል ተሰሚነት መነገድ

፩/ ማንኛውም ሰው የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ባለመሆኑ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፲፮ ለመንግስት ወይም ለህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የተደነገገው የማይመለከተው ቢሆንም፣ ያለውን ወይም እንዳለው ያስመሰለውን ተሰሚነት በመጠቀም በአንድ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ብቻ ሊሰጥ የሚችለውን ልዩ መብት ወይም ጥቅም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ሲል ከሌላው ሰው ገንዘብ፣ ስጦታ፣ እጅ መንሻ ወይም ሌላ ጥቅም የጠየቀ፣ የተቀበለ ወይም እነዚህን በተመለከተ የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ፣ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት እና ከሦስት ሺህ ብር በማያንስ መቀጮ ይቀጣል።

፪/ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው መሰረት በአንድ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ብቻ ሊሰጥ የሚችለውን ልዩ መብት ወይም ጥቅም ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ ገንዘብ፣ ስጦታ፣ እጅ መንሻ ወይም ሌላ ጥቅም የሰጠ ወይም

28. Use of Pretended Authority

Whosoever, promising to perform certain things, solicits or accepts an undue advantage or gift from another:

1/ by pretending to be still on active duty while he has been suspended, transferred, removed or dismissed from or has quitted his employment of public office or public organization; or

2/ by entertaining the belief of becoming a public servant or employee of a public organization in the future; or

3/ by appearing as a public servant, or employee of a public organization while he is not;

shall be punishable, according to the circumstances of the case, with simple imprisonment and fine, or with rigorous imprisonment not exceeding ten years and fine not exceeding Birr ten thousand.

29. Traffic in Private Influence

1/ Whosoever, although not being a public servant or employee of a public organization to be liable under Article 16 of this Proclamation, seeks, exacts a promise or receives sums of money, gifts, presents or other advantages in consideration for exercising his influence, real or pretended, to procure for another any privilege, benefit or advantage which can only be granted by a public servant or employee of a public organization, shall be punishable with simple imprisonment not less than one year and fine not less than three thousand Birr.

2/ Whosoever gives or agrees to give sums of money, gifts, presents or other advantages with the intent to obtain for himself or another person the rights or interests that can only be obtained by public servants or employees of public organizations as provided under sub-article (1) of this Article

ለመስጠት የተስማማ እንደሆነ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀጽ (፩) በተደነገገው መሰረት ይቀጣል።

፫/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፲፮ (፩) ፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ) ወይም (ሐ) የተመለከተውን ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ለማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ስጦታ ወይም ሌላ ጥቅም የሰጠ ወይም ለመስጠት የተስማማ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) በተደነገገው መሰረት ይቀጣል።

## ፴. በምርጫ ላይ የሚሰጥ መደለያ

፩/ ማንኛውም ሰው የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት ያለው ሌላ ሰው በመብቱ በተወሰነ መንገድ እንዲጠቀም ወይም መብቱን እንዲተው ለማድረግ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ገንዘብ ወይም ማናቸውም ሌላ ዓይነት ጥቅም የሰጠ፣ ወይም ለመስጠት ቃል የገባ እንደሆነ፣ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

፪/ የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት ያለው ማንኛውም ሰው በዚሁ መብቱ እንዲጠቀምበት ወይም በአንድ በተወሰነ መንገድ እንዲጠቀምበት ወይም ሳይጠቀምበት እንዲቀር ገንዘብ ወይም ማናቸውም ሌላ ዓይነት ጥቅም የተቀበለ ወይም ለመቀበል የተስማማ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው ቅጣት ይቀጣል።

## ፴፩.ከባድ የእምነት ማጉደል

፩/ ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት የሆነውንና ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዋጋ ያለውን ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ያደረገ፣ ወይም ለሌላ ሰው ያደረገ፣ የወሰደ፣ ያስወሰደ፣ የሰወረ፣ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት ያዋለ ወይም ይህን

shall be punishable with the penalty provided under sub-article (1) of this Article.

3/ Whosoever, with intent to obtain the advantages mentioned under Article 16 (1) paragraph (a), (b) or (c) of this Proclamation, gives or agrees to give a gift or any other advantage to any public servant or employee of public organizations shall be punishable with the penalty provided under sub-article (1) of this Article.

## 30.Corrupt Electoral Practices

1/ Whosoever, directly or indirectly, promises or grants a sum of money, or any other advantage whatsoever to an individual right to vote or to be elected, in order to persuade him to exercise his right to vote or to be elected in a particular way or to abstain from exercising it, shall be punishable with rigorous imprisonment not exceeding five years and fine not exceeding Birr five thousand.

2/ Whosoever possessing the right to vote or to be elected, accepts or agrees to accept a sum of money or any other advantage, in consideration of exercising his right, or exercising it in a particular way, or of abstaining from exercising it, shall be punishable with the punishments provided under sub-article (1) of this Article.

## 31. Aggravated Breach of Trust

1/ Any public servant or employee of a public organization, with the intent to obtain for himself or to procure for a third person an unjustifiable enrichment, appropriates, or procures for another, takes or causes to be taken, misappropriates, uses to his own benefit or that of a third person, or disposes of for any similar act, in whole or in part, a thing or a sum of money which is the property of another and which has been delivered to him in trust or for a specific purpose breaches trust shall be punishable

የመሳሰለውን ማናቸውንም አድራጎት የፈጸመ እንደሆነ ከሦስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከአሥር ሺ.ህ ብር እስከ ሃምሳ ሺ.ህ ብር በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።

፪/ የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት፣ የጥፋተኛው የሥልጣን ወይም የኃላፊነት ደረጃ ወይም በመንግስት፣ በህዝባዊ ድርጅት፣ በህዝብ ወይም በግለሰብ ጥቅም ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛነት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተፈጸመውን ወንጀል ከባድ አድርጎት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከሰባት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከሃምሳ ሺ.ህ ብር እስከ አንድ መቶ ሺ.ህ ብር በሚደርስ መቀጮ ይሆናል።

፫/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) አፈጻጸም፦

ሀ) ተከሳሹ በእምነት እንዲሸጥ ወይም እንዲገዛ ወይም እንዲለውጥ ወይም ለተወሰነ አገልግሎት እንዲያውል የተሰጠውን ገንዘብ ወይም ዕቃ ወይም ዋጋ ያለውን ነገር በተባለው መሠረት ፈፅሞ በምትኩ ያገኘው ገንዘብ፣ ወይም ዕቃ ወይም ዋጋ ያለው ነገር የሌላ ሰው እንደሆነ ይቆጠራል፤

ለ) ተከሳሹ ሲጠየቅ በእምነት ወይም በአደራ የተሰጠውን ገንዘብ ወይም ዕቃ ወይም ዋጋ ያለውን ነገር ለመመለስ ወይም ለመክፈል ወይም ዕቃው ያለበትን ሁኔታ ለማሳየት ወይም ለተገቢው አገልግሎት ያዋለው መሆኑን ለማስረዳት ካልቻለ ንብረቱን ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያልተገባ ጥቅም የማዋል አሳብ እንዳለው ይቆጠራል።

፬/ ለዚህ አንቀፅ አፈፃፀም ሲባል "እምነት ማጉደል" ማለት ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ የሌላ ሰው የሆነውንና ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም በአደራ የተሰጠውን ገንዘብ ወይም ዕቃ ወይም ዋጋ ያለውን ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው የማድረግ፣ የመውሰድ፣ የማስወሰድ፣

with rigorous imprisonment from three years to seven years and fine from Birr ten thousand to Birr fifty thousand.

2/ Where the extent of the advantage received, the degree of power or responsibility of the culprit or the extent of the harm to private, public or State interests, or interest of a public organization renders the crime committed under sub-article (1) of this Article of particular gravity, the punishment shall be rigorous imprisonment from seven years to twenty five years and fine not less than Birr fifty thousand and not exceeding one hundred Birr thousand.

3/ For the application of sub-article (1) and (2) of this Article:

a) presumed to be property of another includes a sum of money, object or thing of value acquired by the accused in exchange of a sum of money, object or thing of value entrusted to him for sale, purchase, exchange or other specific purpose;

c) up on call the accused,unless he proves satisfactorly to produce or repay a sum of money or a valuable object that he taken or prove that he used for actual purpose presumed to be the intent to obtain for him self or to procure for a third person an unjustifiable enrichment.

4/ For the purpose of the implementation of this Article, "breach of trust" means any act with intent to obtain for himself or to procure for a third person an unjustifiable enrichment, appropriates, or procures for another, takes or causes to be taken, misappropriates, uses to his own benefit or that of a third person, or disposes of for any similar act, in whole or in part, a thing or a sum of money which is the property of another and which has been

የመሰወር፣ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት የማዋል፣ ወይም ይህን የመሳሰለውን ማናቸውም እምነት የማጉደል ወንጀልን ያካትታል።

## ፴፪.ከባድ አታላይነት

፩/ ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ አሳሳች የሆኑ ነገሮችን በመናገር፣ የራሱን ማንነት ወይም ሁኔታ በመሰወር ወይም መግለፅ የሚገባውን ነገር በመደበቅ ወይም የሌላውን ሰው የተሳሳተ እምነት ወይም ግምት በመጠቀም፣ በማድረግም ሆነ ባለማድረግ ሌላውን ሰው በማታለል የተታለለው ሰው የራሱን ወይም የሌላውን ሰው የንብረት ጥቅም የሚጎዳ ድርጊት እንዲፈጽም ያደረገው እንደሆነ ከሦስት ዓመት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከሦስት ሺህ ብር እስከ ሰላሳ ሺህ ብር በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ወንጀል የተፈጸመው የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት ወይም በመንግስት፣ ወይም በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝብ ጥቅም ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛነት፣ በወንጀል አድራጊው የስልጣን ደረጃ የወንጀሉን አፈጻፀም ከባድ አድርጎት እንደሆነ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት የሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከአሥር ሺህ ብር እስከ አንድ መቶ ሺህ ብር በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።

፫/ ወንጀሉ የተፈፀመው በሕዝብ አስተዳደር ወይም በሕዝብ አገልግሎት ላይ የሆነ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ ከላይ ከተመለከቱት ንዑስ አንቀፆች በአንዱ መሰረት ያስቀጣል።

## ፴፫. በሙስና ወንጀል የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብና በወንጀሉ ስለመርዳት

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወንጀል የተፈፀመው በሙስና ወንጀል አመንጪነት ከሆነ አግባብነት ያለው በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ህግ

delivered to him in trust or for a specific purpose.

## 32. Aggravated Fraudulent Misrepresentation

1/ Any public servant or employee of a public organization with intent to obtain for himself or to procure for a third person an unlawful enrichment, fraudulently causes a person to act in a manner prejudicial to his rights in property, or those of a third person, whether such acts are of commission or omission, either by misleading statements, or by misrepresenting his status or situation or by concealing facts which he had a duty to reveal, or by taking advantage of the persons erroneous beliefs, shall be punishable with rigorous imprisonment from three to ten years and fine not less than Birr three thousand and not exceeding Birr thirty thousand.

2/ Where the crime stipulated in sub-article 1 of this article is committed by a public servant or employee of public organization of high status or when the advantage obtained or the damage caused to individual, state, public organization or public interest is grave, the punishment shall be rigorous imprisonment from five years to fifteen years and fine not less than Birr ten thousand and not exceeding Birr a hundred thousand;

3/ where the crime is committed against public administrations or services, punishments prescribed in one of the above sub-articles shall be applicable, depending on the circumstances of the case.

## 33.Money Laundering

Where the predicate offence for money laundering is corruption, the crime shall be a Corruption Crime and relevant Money Laundering and corruption laws shall be applicable.

ተፈፃሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ እንደነገሩ ሁኔታ በዚህ አዋጅ መሰረት የሙስና ወንጀል ክስ ይቀርባል።

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፴፬. ተፈፃሚነት ስላላቸው ሕጎች

በወንጀል ህጉ የመጀመሪያ ታላቅ ክፍል ከአንቀጽ ፩ እስከ አንቀጽ ፪፻፴፯ ያሉት ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ ለተመለከቱት የሙስና ወንጀሎችም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

### ፴፭. የተሻሩ ድንጋጌዎች

የወንጀል ሕጉ አንቀጽ ፫፻፸፱፣ አንቀጽ ፫፻፹፩፣ ከአንቀጽ ፬፻፪ እስከ አንቀጽ ፬፻፲፱፣ ከአንቀጽ ፬፻፳፯ እስከ አንቀጽ ፬፻፴፩፣ አንቀጽ ፬፻፷፰ እና የአንቀጽ ፮፻፸፮ (፩) በዚህ አዋጅ ተሽረዋል።

### ፴፮. ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች

የሚከተሉት በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፦

፩/ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ ፮፻፺፮ ድንጋጌዎች፤

፪/ ኃላፊነትን አላግባብ መገልገልን፣ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ማግኘትን ወይም ማስገኘትን እና በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት ማድረስን ለመቅጣት የተደነገጉ የወንጀል ሕጉ ድንጋጌዎች፤

፫/ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች እና የአሠራር ልማዶች።

### ፴፯. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፭ እና ፴፮ ድንጋጌዎች ቢኖሩም ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተፈጸሙ የሙስና ወንጀሎች የሚታዩት በወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች መሠረት ይሆናል።

## PART THREE

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 34. Applicable Laws

The Provisions Articles 1 to 237 of the General Part of the Criminal Code shall be applicable to Corruption Crimes provided for under this Proclamation.

### 35. Repealed Provisions

Article 379, Article 381, Articles 402 to 419, Articles 427 to 431, Article 468 and Article 676 (1) of the Criminal Code are hereby repealed.

### 36. Inapplicable Laws

The following shall be inapplicable with respect to corruption crimes provided for in this Proclamation:

1/ the provisions of Article 696 of the Criminal Code;

2/ the provisions of the Criminal Code relating to abuse of power, receiving or causing another person to receive undue benefits and harming the interests or rights of others;

3/ proclamations, regulations, directives and customary practices inconsistent with this Proclamation.

### 37. Transitory Provisions

Notwithstanding the provisions of Articles 35 and 36 of this Proclamation, corruption cases that are commited before effective date of this Proclamation shall be finalized in accordance with the provisions of the Criminal Code.

**፴፰. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ መጋቢት ፳፭ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚደንት

**38. Effective Date**

This Proclamation shall come into effect on the date of publication in the Federal Negarit Gazzette.

Done at Addis Ababa this 3rd day of April, 2015.

MULATU TESHOME (Dr.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC EPUBLIC OF ETHIOPIA